# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 63 ሐምሌ 23 ቀን 2001 ዓ.ም


ያለመታደል ሆኖ ዛሬ ኢትዮጵያችን መለስ ዜናዊ እራሱ ህግ የሆነባት፣ የዜጎች በነፃነት የመደራጀትና የመንቀሳቀስ መብቶች የታፈኑባት፤ ዘረኛና ግፈኛ አገዛዝ የሚፈነጭባት ሃገር ናት፡፡ ዛሬ በሃገራችን በመያዶች፣ በሙያ ማኅበራት፣ በፖለቲካ ድርጅቶች እና በግል ባለሃብቶች ላይ በወያኔ አማካይነት የሚደርሰው እመቃ የብልሹ አስተዳደርና የዘረኛ አምባገነን አገዛዝ ቀጥተኛ ውጤት ነው፡፡ **ርዕሰ አንቀጽ**

## ወያኔ የመከላከያን ከፍተኛ በጀት ለትግራይ ክልል እንደ ተጨማሪ ልዩ በጀት አድርጎ ይጠቀማል፡፡ በሰራዊቱ ውስጥ ዘረኛ መድሎን ይፈጽማል፡፡ የትግራይ ሪፑብሊክ ምስረታ ህልሙንም አልረሳም፡፡

በአሁኑ ጊዜ 85% የሚሆነው የመከላከያ ሠራዊት ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ በትግራይ ክልል ሠፍሮ ይገኛል፣ይህንንም አጋጣሚ በመጠቀም :-

1. ለሠራዊቱ ቀለብ አቅርቦት ያለ ጨረታ ከአዛዧች ጋር በመመሳጣር፣ የትግራይ ሰዎች ብቻ እንዲያቀርቡ ተደርጓል። አቅራቢ ከሆኑትም መሀል አቶ ጉዕሺ፣ ወ/ሮ ዘውዴ ፣ አቶ ስብሀት ፣ ወ/ሮ አዲስ፣ አቶ ገብረስላሴ፣ አቶ ሃጎስ በመባል የታወቁ ሰዎች ይገኙበታል፡፡ ለሰራዊቱ የሚያቀርቡትም አትክልት ፣ በርበሬ፣ የወጥ እህሎችና ሥጋ፣ ዱቄት ፣ ዘይት ወዘተ. መሆኑ ታውቋል። አቅራቢዎቹ የትግራይ ሰዎች አቅርቦቱም ከትግራይ ክልል እንዲገዛ ተደርጓል።
2. ሰራዊቱ በከፍተኛ ቁጥር ትግራይ ላይ በመስፈሩ ብቻ ምን ያህል የክልሉን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንደጠቀመ አንድ ምሳሌ እንስጥ፡፡ የወያኔ አንድ ወታደር በቀን 8 ዳቦ ይበላል፡፡ ይህም ማለት ወደ መቶ ሽህና ከእዛም በላይ የሚቆጠረው በትግራይ ውስጥ የሰፈረው ሰራዊት በአማካይ በትንሹ በቀን 800000 ዳቦ ያስፈልገዋል ማለት ነው፡፡ በቀን ይህን ያህል ዳቦ የማቅረብ ስራ ብቻ ምን ያህል ኢንቨስትመንት የሚያስፈልገው እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡ ወያኔ ሰራዊቱ በሆዱ እንዳይከፋበት ካለው ፍላጎት ለምግብ ከፍተኛ ወጪ ያደርጋል፡፡ ካዳቦ ውጭም በእዚሁ በትግራይ ክልል ውስጥ ሰራዊቱን መሰረት በማድረግ የሚመረተው የተለያየ የምግብ ውጤትና ሽያጭ በገንዝብ ሲለካ በብዙ መቶ ሚሊዮኖች ብር የሚቆጠር ይሆናል፡፡

**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## የዘራፊው መለስ ዜናዊ ቡድን አገሪቱን የመቸብቸብ ፖሊሰውን አጠንክሮ እየገፋበት መሆኑ ታወቀ።

«ረዩተር» የተባለው የዜና ወኪል ይፋ ባወጣው ዘገባ መሠረት በኢንቬስትመንት ስም ከአንድ ሚሊዮን ተኩል ሄክታር በላይ መሬት ለውጭ አገር ዜጎች (በተለይም ከአረብ ና ከመካከለኛው እስያ ለመጡ) እንደሚሰጥ ዘግቧል። የእነዚህ አገራት ባለሃብቶች በአገራቸው የመሬት ችግር ስላጋጠማቸው ለአገሩ አሳቢ መንግስት ወደ ሌለባት ኢትዮጵያ በመጉረፍ ላይ ሲሆኑ፣ የወያኔው ቁንጮ መለስ ዜናዊም አያቶቹ በባንዳነት ከጣሊያን ጎን ተሰልፈው የወጉዋትን አገር መሬት፣ እንደልቡ እየቸበቸበ ገንዘብ በውጭ ባንኮች ውስጥ በማከማቸት ላይ መሆኑ ይታወቃል።

የውጭ ባለሀብቶቹ በጣም ትንሽ ገንዘብ ይዘው በመምጣት መሬት እንዲሰጣቸው የሚደረገው አንድም ለፖለቲካ ፍጆታ ሌላም ይዘዋት የሚመጡት ጥቂት ዶላር በውጭ ምንዛሬ እጥረት እየተሰቃየ ለሚገኘው ለመለስ አምባገነን አገዛዝ ድጎማ ትጠቅማለች በሚል ሰበብ ሊሆን እንደሚችል የሚናገሩ አሉ።

አስተያየት ሰጪዎቹ በማከልም ከደሀው ገበሬ እየተነጠቀ ለውጭ ባለሀብቶች የሚሰጠው መሬት ለአገሪቱ ገበያ የማይቀርብ መሆኑ እና አልሚዎችም በቂ የእርሻ ቴክኖሎጂ እውቀት የሌላቸው መሆኑ እየታወቀ የመለስ ዘረኛ አገዛዝ ግን «እኔ ከሞትኩ …» በሚል ስሌት የአገሪቱን መሬት እየቸበቸቡ መሆኑን ገለፁ።

በተያያዘ ዜናም በዚህ አመት ከ12 ሚሊዮን በላይ ህዝብ ለችጋር እንደሚጋለጥ የዓለማቀፍ ድርጅቶች እያስጠነቀቁ ነው። የኢትዮጵያን ህዝብ በቀን ሶስት ጊዜ እንዲበላ አደርገዋለሁ ሲል የነበረው ዘረኛው መለስ ዜናዊ፣ ከ18 ዓመታት የሥልጣን ጊዜ በኋዋላ ህዝቡን ልጆቹን በፈረቃ ማብላት መቀጠሉ ይታወቀል። ሰሞኑን ያለም የምግብ ፕሮግራም ባወጣው ዘገባ በኢትዮጵያ ቤተሰቦች በፈረቃ መብላት መጀመራቸውን መዘገቡ ይታወሳል።

## የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከአገር ጥቅም ይልቅ የወያኔን ቡድንና የግለሰቦችን ስሜትና ፍላጎት የሚያስፈጽም መሥሪያ ቤት መሆኑን ተጋለጠ

ኢትዮጵያዊው ዲፕሎማት አቶ ዘበነ ኃ/ማርም ገነሜ በወያኔ ካድሬዎች በደረሰባቸው ወከባ ሥራቸውን ለቀው ተሰደዋል። በየመን የኢትዮጵያ ኢምባሴ ውስጥ በተለያዩ የኃላፊነት እርከኖች በሰሩበት ወቅት የደረሰባቸውን የመብት ረገጣ በመዘርዘር «ነግ በኔ» በማለት ልምቸውን ለሌሎች ዲፕሎማቶች አስተላለፉ።

ዲፕሎማቱ ዘነበ ኃ/ማርያም ገነሜ በጽሁፋቸው ላይ እንደገለጹት ለበርካታ ዓመታት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ላይ ነግሶ የሚገኘው የገዥው ፓርቲ ዋናው ተዋናይ ስዩም መስፍን እራሱ ፍጹም አዛዥ ሆኖ ሌሎች ጫጩት ካዴሬዎች እንዲፈለፈሉ እና ጭፍሮችም እንዲመለመሉ በማድረግ የግል ሃብት እያካበተ፤ ስልጣን ሙጥኝ ብሎ ጡረታ የማይወጣው በዓለም የመጀመሪያው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኖ ቀጥሏል ብለዋል።

**ወደ ገጽ 2 ዞሯል**

## አሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሚስ ሂላሪ ክሊንተን በሰባት የአፍሪካ አገሮች ጉብኝታቸው ኢትዮጵያን አለመማካተታቸው ወያኔን ያሳፈረ መሆኑን ኢትዮጵያውያን ገለጹ

በአሜርካ የፕሬዚዳንት ምርጫ ወቅት የወያኔ አገዛዝ ለሚስ ሂላሪ ክሊንተን መመረጥ በአላሙዲን በኩል የገንዘብ ድጋፍ ማድረጉ በጊዜው በስፋት መዘገቡ ይታወሳል፡፡ ያ ሳይካ ቀርቶ ፕሬዚዳን አባማ ተመረጡ፡፡ ቀጥሎ ሂላሪ ክሊንተን የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር ሆነው ሲሾሙ በኢትዮጵያ ህዝብ ገንዘብ የሚተዳደሩት እንደ አይጋ ፎረም የመሳሰሉት ድህረ ገጾች «ሂላሪ መጣች» በሚል ርእስ በጥር 2001 ሂላሪን በማወደስ አለቃቸውን ፕሪዚዳንት አባማን ግን የሚያሳንስ የሚከተለውን አሳፋሪ ግጥም ገጥመውላቸው ነበር።

ለአጋዴን የተነባው ያዞ እንባ  
ትርፍ አልሰጠ የረባ  
የቅንጅት ባቡር ባይቀናቸው  
መንጠልጠል አይደል ስራቸው  
ደግሞ ዘለሉ በውድቅት  
በይቻላል ባቡር ቀድመው ለመገኘት  
እድሉን ሊፈትን ባሜሪካ  
ብይዋን አሾሩ አንከባለሉ  
በአባማ ድል ማለሉ

ብቻ ምን ያደርጋል አቦ  
ማትሆነልል በእዝቅ ዳቦ  
ተገፍታ ማትገፋ ማትታለል በጮሌ  
እንፈልግ መርዶ ነጋሪ  
መጣች ተሹማ ሂላሪ  
ስቴት ዲፓርትመንት ስትመራ  
ቦታ የለም ላምታች ለፉገራ  
አይ አምታቾቼ ብልጣ ብልጡ  
አባማ አባማ ብለው ቀለጡ

ወያኔ ይህንን የውጭ ጉዳይ ሚስትሯን ከፕሬዚዳንቱ የሚስበልጥ ግጥም ቢያስገጥምም ሂላሪ ክሊንተን ግን በወያኔ የቀረበላቸውን መወድስ ባለመስማት ጎረቤት አገር ኬንያን፣ ደቡብ አፍሪካን፣ ዲሞክሪቲክ ኮንጎን፣ ላይቤሪያን፣ ናይጀሪያን ፣ ኬፕ ቨርዴንና አንጎላን በሚቀጥለው ሳምንት ሲጎበኙ፣ የአፍሪካ መዲናን ኢትዮጵያን አለመጎብኘታቸው ለወያኔ ትልቅ የዲፕሎማሲ ኪሳራ መሆኑን አስተያየት የሰጡን ሰዎች ገልጸዋል።

ባለፈው ወር ፕሪዚዳንት አባማ ጋናን በጎበኙበት ወቅት እንደመለስ ዜናዊ ላሉ ፈላጭ ቆራጭ ገዚዎች ጥብቅ ማስጠንቀቂያ መላካቸው ይታወሳል።

## የመለስ ዜናዊ የሚመራው ዘረኛ አገዛዝ በወገኖቻችን ላይ የፈጸመውን የዘር ማጥፋት ወንጀል የሚያጋልጥ ስብሰባ ተካሄደ

ጄኖሳይድ ዎች ፕሬዚዳንት ግሪጎሪ ስታንቶንና የሰብአዊ መብት ታጋዩ ኢትዮጵያዊው አባንግ ሜቶ የተዘጋጀው ይህ መድረክ የዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ አገዛዝ በግፍ የጨፈጨፋቸውንው ንጹን ዜጎች ምስል በማሳየት መለስ ዜናዊ የሚፈጽማቸውን ወንጀሎች ለአለም አቀፍ ህብረተሰብ ዕይታ በማቅረብ ትኩረት ለመሳብ እንደሆነ የገለጹት አዘጋጆች በዋሽንገትንና አካባቢው የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ፈረንጅ ጓደኞቻቸውን ይዘው እንዲመጡ ጥሪ አስተላልፈዋል ::

የብሄር ብሄረሰቦችን እኩልነት የሚያከብር ሥርዓት በአገሪቱ አስፍኛለሁ እያለ የሚኩራራው የወያኔ አገዛዝ አገሪቷ በቅርብ ጊዜ ታሪኳ አይታው የማታውቀውን አይነት ዘረኛ ፖሊሲ በመንደፍ በአገዛዙ ላይ ምሬት ያላቸውን ተቃዋሚ ዜጎች ለመጨፍለቅ በሚወስደው ፋሽስታዊ እርምጃ በጋምቤላ፣ በኦጋዴንና በሌሎች የተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ከፍተኛ ሰቆቃዎች እንደፈጸመና አሁንም በመፈጸም ላይ እንደሚገኝ በቅርቡ ያወጣው የጻረ ሽብረተኛ ተብዬው አዋጅም ለሚፈጸመውን ሰቆቃ ህጋዊ ሽፋን ለመስጠት የታለመ መሆኑን ብዙዎች ይስማሙበታል::

ወያኔ በወገኖቻችን ላይ የሚፈጽመውን ይህንን ወንጀል ለአለማቀፍ ችሎት ለማቅረብ ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ካሉት እንደነ ህይውማን ራይትስ ወች፣ አሚንስቲ እንተረናሽናልና ጂኖሳይድ ዎች የተውጣጡ ሰዎች በተገኙበት በዚህ ስብሰባ በርካታ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

**ከወያኔ ዘረኛ አካሄድ መማር የሚገባን የወያኔ ዘረኛት ባስመረረን ቁጥር እያንዳንዳችን የራሳችንን በዘር ላይ የተመሰረተ አጥር በመስራት ችግሩን ልንፈታወ የማንችል መሆኑን ነው። የዘር አጥር መገንባት የወያኔ ዘረኛነት በጋራ ለመታገል የምንችልበትን ጉልበት በታትነን ከሃገሪቱ ህዝብ 6 በመቶ የማይሞላውን ትግራይን እወክላለሁ ለሚል ኋላ ቀር ቡድን ራሳችንን መቀለጃ በማድርግ ለሚደርስብን ውርደት እራሳችንን ተባባሪዎች አደርገን ማቅረብ ይሆናል አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ**

### ወያኔ በመያዶች ላይ የሚፈጽመው ጥቃት በሰብአዊ መብቶችና በዜጎች ነጻነት ላይ የከፈተው አጠቃላይ ጥቃት አካል ነው

የአገራችን ምስኪን ድሃ ገበሬ የሚቀምሰው እህልና ውሃ አጥቶ ሲረግፍ በሚኒሊክ ቤተመንግስት የመሸጉ የአገዛዞች ሹማምንት በውስኪና ሻምፓኝ ሲራጩ ከርመዋል፡፡ በየጊዜው እየተመላለሰ የወገኖቻችንን አቅም ከማድከም ባሻገር የሺዎችን ህይወት በቀሰፉ የችጋር ወቅቶች ለድሃው የደረሱለት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (**መያዶች**) ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት መያዶች የድሃው አጋርና ባለውለታዎች ናቸው፡፡

ከአስቸኳይ የህይወት አድን እርዳታ ባሻገርም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ድሃ አገሮች ውስጥ መያዶች የዘላቂ ልማት አጋር ሊሆኑ እንደሚችሉ ተደጋግሞ የታየ ጉዳይ ነው፡፡ ነፃነትና ልማት የማይነጣጠሉ መሆናቸው በመገንዘብ መያዶች ተግባሮቻቸውን «መብት-ተኮር» እና «ፍላጎት-ተኮር» ማድረጋቸው መወደስ የሚገባው መሻሻል ነው፡፡ በእነዚህ የተሻሻሉ አካሄዶች በመመራት ዜጎቻችን ከድህነትና ከረሃብ ለዘለቄታው እንዲገላገሉ መብቶቻቸውን ማስከበር እንዳለባቸው ለማስተማር ሞክረዋል፡፡ በተጨማሪም እንደቀድሞው «የሚበጅህን አውቅክልሃለሁ» ከማለት ተቆጥበው ከተጠቃሚው ፍላጎትና ከአካባቢ እውቀት ለመነሳት ጥረት እያደረጉ ነው፡፡ ከዚህ ረገድ በህፃናት፣ በሴቶች፣ በአናሳ ዘውጎች እና በህሙማን መብቶች ዙርያ የሚወደሱ ተግባራትን አከናውነዋል፡፡ መያዶች ይህንን አኩሪ ሥራ የከወኑት የመብት ጉዳይ ፈጽሞ እንዲነሳ የማይፈልግ አገዛዝ የሚያደርግባቸውን ያልተቋረጠ ጫና እየተጋፈጡ የመሆኑ ሃቅ ይበልጥ እንድናከብራቸውና እንድናበረታታቸው ያደርገናል።

በ1997 ምርጫ በርካታ መያዶች ህዝብን በማስተማርና በማንቃት ሥራ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መሳተፋቸው ወያኔን አበሳጭቶታል፡፡ በዚህም ምክንያት ከምርጫ 97 ወዲህ ወያኔ በመያዶች ላይ በግላጭ ዘምቶባቸዋል፡፡ ወያኔ መያዶችን ለመቆጣጠር ዘንድሮ መላውን ዓለም ያስቆጣ ህግ ማውጣቱ ይታወሳል። በአዲሱ ህግ መሠረት የኢትዮጵያ መያዶች ሥራ-አስኪያጆቻቸውን እስከ መሾምና መሻር የዘለቀ የአገዛዙ ቀጥታ ቁጥጥር የሚደረግባቸው በመሆኑ «መንግሥታዊ ያልሆኑ» የሚለውን ስያሜ ራሱ ዋጋ አጥቷል፡፡ ከዚህም በላይ ከወጪዓቸው አስር በመቶ በላይ ከውጭ አገር በሚገኝ እርዳታ የሚደጎሙ ከሆነ አንዳችም የመብት ጉዳይ ውስጥ እንዳይገቡ አዲሱ የአፈና ህግ አግዷቸዋል፡፡ እንደ አገዛዙ አመክኖ ከሆነ የአትዮጵያ መያዶች መድሃኒት መስጠት እንጂ ስለህሙማን መብትና ግዴታ ማስተማር፤ የውሃ ጉድጓድ መቆፈር እንጂ ለጉድጓጉ ዘለቄታዊ ጥበቃ ተጠቃሚዎችን ማደራጀት፤ ምግብ መስጠት እንጂ ስለ መኖር መብት ማስተማር አይችሉም፡፡ ይህንን ህግ ያወጣው የበጀቱ አንድ ሶስተኛ እርዳታ የሆነውና በእርዳታ ሱስ የነፈዘው የወያኔ አገዛዝ መሆኑ የዘመኑ ምፀት ነው፡፡

ሐምሌ 11 ቀን 2001 ዓ.ም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ውስጥ ይንቀሳቀሱ የነበሩ የአርባ አንድ መያዶች የሥራ ፈቃድ በአንድ የቡድን ኃላፊ ፊርማ ተሰርዘዋል፡፡ ይህ ትዕቢትና ንቀትን ጭምር ያስተላለፈው የቀላጤ ትዕዛዝ ለአርባ አንዱም መያዶች የሥራ ፈቃድ መሰረዝ የዘረዘራቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. አርሶ አደሩ የግብርና ግብዓቶችንና ማዳበሪያ እንዳይጠቀም የግብርና ፓሊሲውን በሚፃረር ሁኔታ ቅስቀሳ በማድረጋቸው፤
2. ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዳይወገዱ በባህል ስም ሕዝቡን በመቀስቀስ በሕገወጥ ተግባር በመገኘታቸው፤

ለመያዶቹ ፈቃድ መሰረዝ የተጠቀሱት ሁለቱም ምክንያቶች «ቅስቀሳ» መሆናቸው እና አርባ አንዱም መያዶች በተፈጥሮ ሃብትና ባህል ጥበቃ ሥራ ላይ የተሰማሩ የነበሩ መሆናቸው የወያኔ ትኩረት ምን ላይ እንደሆነ ያመላክታሉ፡፡

ለመሆኑ «ቅስቀሳ» ምንድነው? ማስተማር መቀስቀስ አይሆንምን? እነዚህ መያዶች ያደረጉት ቅስቀሳ አማራጮችን ማስተዋወቅ ከሆነ ህግ ባለበት አገር ቢሆን ኖሮ የሚበረታታ ተግባር እንጂ «ህገ-ወጥ» አይሰኝም። የወያኔ «የግብርና ፓሊሲ» ገበሬውን ከድህነትና ረሃብ ያላላቀቀ በመሆኑ አማራጮችን መፈለግ የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ነው፡፡ መያዶቹ ከወያኔ ፓሊሲ የተለየ አማራጭ አቅርበው «ቀስቅሰው» ከሆነ ሊመሰገኑ በተገባ፡፡ የተሻለውን መምረጥ የወያኔ ሹመኞች ሳይሆን የገበሬው መብት ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግም በማዳበሪያና «ምርጥ ዘር» ሽፋን ወያኔ የሚሰራቸው ደባዎች ገበሬውን አማረዋል፡፡ የወያኔ ቱጃሮች ከመርካቶ እህል በረንዳ በጅምላ እየገዙ «ምርጥ ዘር» እያሉ በአራትና አምስት እጥፍ ዋጋ ለገበሬው እየሸጡ በገበሬውም በግብርናውም ላይ ስለሚፈፅሙት ደባ በቅርቡ በዝርዝር መጋለጡ አይቀርም፡፡ የኬሚካል ማዳበሪያም ጉዳይም ቢሆን ከግዢ አንስቶ እስከስርጭት ድረስ በወያኔ ድርጅቶች የተያዘ «የወተት ላም» መሆኑ ይታወቃል፡፡ ወያኔ በግልፅ «ማዳበሪያና ቴሌን» አትንኩብኝ ያለውም ለዚሁ ነው። አሁንም ህግ ባለበት አገር ቢሆን ኖሮ ከኬሚካል ማዳበሪያ ወደ ተፈጥሮ ማዳበሪያ መሸጋገርን ማሰብ የሚበረታታ ሙከራ እንጂ በጭፍኑ የሚወገዝ አይደለም፡፡ አሁንም የቱ እንደሚሻል መወሰን የእያንዳንዱ ገበሬ የግል ውሳኔ መሆን ይኖርበታል፡፡ ወያኔ የኢትዮጵያን ገበሬው ሲሻው የስልጣኑ ምንጭ፤ ሲሻው ደግሞ የሚበጀውን እንኳን የማያውቅ የእእምሮ ድኩም አድርጎ ያቀርበዋል፡፡

ከላይ «ህግ ባለበት ሃገር ቢሆን ኖሮ» ብለናል፡፡ አዎ ህግ ባለበት ሃገር ሥልጣን የያዙ አካላት እንዳይባልጉ፤ በሙስና እንዳይበሰብሱ ለህዝብ ትምህርት የሚሰጡ፤ አማራጭ የልማት ሃሳቦችን ይዘው የሚቀርቡ መያዶች ይበረታታሉ እንጂ አይጠቁም፡፡ በአካባቢ ጥበቃ፣ በማኅበራዊና የኢኮኖሚ ችግሮቻቸው ላይ ዜጎች አቅማቸውን፣ ልምዳቸውን፣ እውቀታቸውንና ጉልበታቸውን አስተባብረው መፍትሄ እንዲፈልጉ የሚያስተባብሩና ድጋፍ የሚሰጡ መያዶች የለውጥና የእድገት አጋር ተደርገው ስለሚታዩ ህጋዊ ጥበቃና እንክብካቤ ይደረግላቸዋል፡፡

ያለመታደል ሆኖ ዛሬ ኢትዮጵያችን መለስ ዜናዊ እራሱ ህግ የሆነባት፣ የዜጎች በነፃነት የመደራጀትና የመንቀሳቀስ መብቶች የታፈኑባት፤ ዘረኛና ግፈኛ አገዛዝ የሚፈነጭባት ሃገር ናት፡፡ ዛሬ በሃገራችን በመያዶች፣ በሙያ ማኅበራት፣ በፖለቲካ ድርጅቶች እና በግል ባለሃብቶች ላይ በወያኔ አማካይነት የሚደርሰው እመቃ የብልሹ አስተዳደርና የዘረኛ አምባገነን አገዛዝ ቀጥተኛ ውጤት ነው፡፡

ግንቦት 7 በነፃነት የሚደራጁና የሚንቀሳቀሱ መያዶችና ሌሎች ሲቪል ማኅበራት ኢትዮጵያ ድህነትን ድል የመታች፣ በፍቅር የተሳሰሩ ነፃ ዜጎች ያሏት ሃገር ለማድርግ በሚደረገው ጥረት ቁልፍ ሚና ከሚጫወቱት ተቋማት መካከል ይመድባቸዋል። ለዚህም ነው ወያኔ በመያዶችና በሌሎች የሲቪል ማኅበራት ላይ የሚወስዳቸውን ማናቸውንም የአፈና እርምጃዎችን የሚኮንነው፡፡ ከዚህም ጽኑ እምነታችን በመነሳት በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በሚገኙ መያዶች ላይ የተወሰደውን የወያኔ አሳፋሪ የእብሪት እርምጃን አጥብቀን እንኮንናለን፡፡ በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጭ የሚገኙ ለመብት መከበርና ለእድገት የቆሙ የፖለቲካና ፖለቲካዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ዜጎች በሙሉ ይህን ግፈኛ የወያኔ እርምጃ እንያዲወግዙና እንዲታገሉ፤ ለወያኔ ዋነኛ መጽዋች ለሆኑ የምዕራብ መንግስታትና ዓለምአቀፍ ድርጅቶች ይህንን አፋኝ የወያኔ ድርጊት በማጋለጥ እንዲተባበሩ የግንቦት 7 ንቅናቄ ጥሪ ያቀርባል፡፡

ወያኔ በመያዶች ላይ የከፈተው ይህ ጥቃት በአጠቃላይ በዜጎች ላይ የከፈተው ጥቃት አካል መሆኑን አውቀን የመያዶችም ሆነ የሌሎች ሲቪል ድርጀቶች መብቶችን የማስከበር ጥያቄ በሃገራችን ውስጥ ፍትህ፣ ነጻነትና ዲሞክራሲ እንዲሰፍን የሚደረገው ትግል አካል መሆኑን በመረዳት፤ ሁላችንም በጋራ የግፍና የአፈናውን ምንጭ ለማድረቅ እንድንታገል ግንቦት 7 ጥሪ ያቀርባል፡፡

ነፃ ሲቢክ ማኅበራት ያበቡባት፤ ዜጎች በነፃነት የሚደራጁባት ከድህነትና ሰቆቃ የተላቀቀች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ በቁርጠኝነት እንታገል!!

## የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከአገር ጥቅም ይልቅ የወያኔን ቡድንና የግለሰቦችን ስሜትና ፍላጎት የሚያስፈጽም መሥሪያ ቤት መሆኑን ተጋለጠ

ከገጽ 1 የዞረ

ስንቱን ምሁራንና አዋቂዎችን ያፈራችና እያፈራች የምትገኘው ኢትዮጵያ ዛሬ በተጫናት ዘረኛ አምባገነን ሥርአት በተፈጠሩ እንደ ስዩም ባሉ ራሳቸውን ሊቅ አድርገው በሚቆጥሩ ጊዜ ያለፈባቸው እድሜ ጠገቦች ስትደቆስ ማየቱ የሚያሳዝን ነው የሚሉት ዲፕሎማቱ፣ የዲፕሎማሲ ሥራው ሁሉ በተዋረድ በጠባብ የቡድን ጥቅም ማስጠበቅ ላይ የሚዳክር ነው ሲሉ አጋልጠዋል።

የኢትዮጵያን ኤምባሲዎችና የቆንስላ ጽ/ቤቶች በአንድ ብሄር ፍጹም የበላይነትና ሙያዊ ብቃት የሌላቸው ካድሬዎች ፍላጎት ማስፈጸሚያ በመሆናቸው፤ ችሎታና የአገር ፍቅር ያላቸው ዲፕሎማቶች ሥራቸውን በነጻነት ማከናወን በማይችሉበት ደረጃ ላይ መሆናቸውን ተናግረዋል። በዘር በተመለመሉ ካዴሬዎችና አጫፋሪዎች ስድብና ማስፈራያ የማይመለስ ዲፕሎማት በክብር የተሰጠውን የመጓጓዣ ሰነድ (ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት) ተነጥቆ ወደ ሚወዳት አገሩ ተመልሶ እንዳይገባ ይደረጋል ብለዋል።

ከ1997 ዓ.ም ምርጫ በኋላ በውጭ ጉዳይ መ/ቤት ሠራተኞች ላይ በተደረገ ግምገማ በርካታ ዲፕሎማቶች በፖለቲካ አመለካታቸው ምክንያት መባረራቸውን እና እንደ ኒውዮርክና ዋሽንግተን በመሳሰሉት ኢምባሲዎች የሚሰሩ ዲፕሎማቶች ቢሮዎቻቸው በላያቸው ላይ ታሽጎባቸው እንደነበር ተናግረዋል።
በግል ስለደረሰባቸው አሳዛኝ ሁኔታም ዲፕሎማቱ ሲያብራሩ «በሥራ በተመደብኩበት የመን በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ውስጥ የሰንአ-ፎረም፣ የፖለቲካ ጉዳዮች፣ የቢዝነስና ኢኮኖሚ ዘርፍ፣ የቆንስላ አገልግሎት፣ ወደ ገጽ 4 ዞሯል



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ሃይለ ሀሳብ

## ከወያኔ ዘረኛ እምነቶችና ድርጊቶች ምን እየተማርን ነው። የዘረኛነትን አደጋ ለመታገል ምን ማድረግ እንችላለን?

አንዳርጋቸው ጽጌ (ሐምሌ 5 ቀን 2001 ዓም፣ ሚነሶታ አሜሪካ በግንቦት 7 ህዝባዊ ስብሰባ ላይ የቀረበ ንግግር)

**ካለፈው የቀጠለ**

እስቲ አስቡት ከፊት ለፊታችን የምናየት፣ የውበት ጸዳልዋ መንገዱን ሞልቶ በሩቁ ያደነቅናት ወጣት አጠገባችን ደርሳ በደንብ ስናውቃት ኦሮሞ/አማራ/ትግሬ ወይም ከእኛ ዘር ውጭ በመሆንዋ ብቻ ውበቷ ትርጉም የሚያጣ ከሆነ፤ በንጽህና ሳቃቸው ልባችንን የሚሰርቁት የህጻናት ድምጽ የሚነካን ህጻናቱ ከራሳችን ዘር መምጣቸውን ስናውቅ ብቻ ከሆነ፤ ለልጇ ሞት አምራ የምታለቅስ እናት ሃዘኗ የሚሰማን የእኛ ከምንለው ዘር ብቻ ከመጣች ከሆነ፤ እስቲ አስቡት ምን አይነት ሃገርና ማህበረሰብ እየፈጠርን ነው? እውነትም በጥላቻ የተሞላ የመውደድና የማፍቀር አቅማቻን የተሰለበበትን በስቃይ የተሞላውን ምድራዊ ገሃነብ እየገነባን ነው ማለት ነው።

ከልቤ ነው፣ ከወያኔ ዘረኛ እምነትና ተግባር ተምረን በግዜ ሁላችንም ብሄረሰብን/ዘውግን ወይም ዘርን በሚመለከት የያዝነውን የፖለቲካ ቅኝት ለመፈተሽና በእዚህ ከዘር ጋር በተያያዘ ፖለቲካ ውስጥ ያሰፈሰፈውን ለአንዳችንም የማይበጅ የጥፋት መርዝ በግዜ ካልነቀልነው የኢትዮጵያና የዜጎቿ መከራና ጣር ማለቂያ አይኖረውም። አሁን ከምናየው ደረጃ በሽዎች እጥፍ የሚያድግበትን ሁኔታ ልንፈጥር እንችላላን የሚል ስጋት አለኝ።

ወያኔ ዛሬ እራሱ በተግባር እያዋለው ያለው ዘረኛነት እየቀሰቀስ ያለው ቁጣ የተለያዩ መገለጫዎች አሉት። አንዱና አስፈሪ የሆነው መገለጫ የዘር ስሜትን ማጠናከር ነው። በዘር ላይ የተመሰረተን ጥላቻ ማስፋፈትን ነው።

ወያኔ የራሱን የዘረኛት እምነት ለማስፋፋትና ዘረኛ የሆነውን አገዛዙን ለማጠናከር የቻለው በሃገራችን ውስጥ የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች፣ ወይም ዘውጌ ማህበረሰባት የመኖራቸውን ሃቅ ለእኩይ አለማው መጠቀሚያ በማድረግ ነው። ሃገራችንም እነዚህን ዘውጌ ማህበረሰባት ለማሰባሰብ ይሁን የተሰባሰቡትን ይዞ ለመቀጠል የቻለችበት ታሪኳ፤ በስቃይ፣ በመከራ፤ በእንባና በደም የተለወሰ አንድ አሳዛኝ ገጽታ ያለው መሆኑን ሃቅ ለመሰሪ አላማው መገልገያ በማድረግ ነው። ይህንንም የታሪክ ገጽታ ወያኔ መዘርጋት ለፈለገው ዘረኛ ስርአት መጠቀሚያ ለማድረግ ቆርጦ በመነሳቱ ነው።

ወያኔ በኢትዮጵያ ውስጥ የተቀሰቀሰውንና ለረጅም ዘመናት የቆየውን ፍትሃዊ የሆነ የዘውጎች/ የብሄር ብሄረሰቦች የእኩልነት ጥያቄ ወደ ዘር ጥላቻ እንዲቀየር በማደረግ የኢትዮጵያን ህዝብ ከፋፍሎ ለመግዛት ተጠቀመበት። ወያኔ ብሄር/ ብሄረሰቦች ወይም የዘውግ ማህበረሰቦች ያነሷቸውን፣ **በማእከላዊ መንግስት ጉዳዮች ጭምር የመወሰን መብት ጥያቄ፤** ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ፣ ቋንቋን የመጠቀም ባህልን የማበልጽግ ጥያቄ፣ በዋንኛነት ይህ ጥያቄ ከሚመለከታቸው ኢትዮጵያውያን ዜጎች ቀምቶ፤ ዘመናዊነት ያልቀበረውን የጨለማ ዘመን የትግራይ መሳፍንቶች የስልጣንና የጥቅም ሽኩቻ በአዲስ መልኩ ነፍስ ዘርቶበት ከደደቢት በረሃ ተንደርድሮ አዲስ አበባ ከምኒልክ ቤተመንግሰት ከች ያለ ድርጅት ነው።

ዛሬ በሃገራችን ዜጎች ወይም የሰው ልጆች ምርጫ ሳይኖራቸው የተወለዱበትን የዘውግ ቡድን/ዘር/ ብሄረሰብ፣ ማለትም ኦሮሞነትን፣ አማራነትን፣ ጉራጌነትን፣ ሲዳማነትን፣ አኝዋክነትን መለያ ያደረገ ጥቃት እየደረሰባቸው ነው። የመገደል፣ የመታሰር፣ የመዋረድ፣ ምክንያቶች በዘር መለያ የሚታደል ሆኗል። የመደህየት፣ የመሰደድ፣ በበሽታ የማለቅ እድላቸው፣ በዘር ላይ የተመሰረተ ሆኗል። ለስልጣን፣ ለሃብት፣ ለከፍተኛ ትምህርት የሚታጨበት ወይም የማይታጨበት እድል በዋንኛነት በዘር ማንነት ላይ የተመሰረተ ነው። ይህ ሁኔታ እኛና እነሱ የሚልን መከፋፈል መፍጠሩ የማይቀር ነው። እራሱን ተጠቃሚ አድርጎ የሚያየው የአንድ ዘውግ ቡድን አገኘሁት የሚለውን ጥቅም በማናቸውም ኪሳራ ለመከላከል ሲሞክር፣ ከጥቅም የተገለለውም ደግሞ በማናቸውም ኪሳራ የተቀማውን ጥቅምና መብት ለማስመለስ ሲታገል መጨረሻው ፍጥጫ ግጭትና እልቂት እንደሚሆን የታወቀ ነው። ወያኔ በሃገራችን የዘረጋው ዘረኛ ስርአት እንዲህ አይነቱን ሁኔታ በኢትዮጵያ ውስጥ በማንገስ ላይ የተመሰረተ ነው።

ወያኔ በጉልበት የያዘውን ስልጣንና ከእዚህም ስልጣን ጋር ተያይዞ የሚያኪያሂደውን አጅግ ዘግናኝ የሆነ ዘረፋ፣ ዘረኛ በሆነ መንገድ ከመግፋት ሌላ አማራጭ የለውም። ይህ ዘረኛነት ሌላውን በዘር ለይቶ መበደል ብቻ ሳይሆን፤ በእዚህ በደል የተነሳ በሌላው ወገን የሚነሳውን ፍትሃዊ ተቃውሞ መቋቋም እችላለሁ ብሎ ወያኔ የሚያምነው ሁሉንም የትግራይ ተወላጅ በወያኔ ስርአት ተጠቃሚ እንደሆነ አድርጎ እንዲያምን ሌላውም ህዝብ ይህን እውነት ነው ብሎ እንዲቀበል በማድርግ ነው። የትግራይ ህዝብ ህልውና፣ ከወያኔ ህልውና ጋር የተቆራኘ እንደሆነ ያለወያኔ የትግራይ ህዝብ መብቱም ጥቅሙም ህልውናውም እንደማይኖር ለማሳመን በመጣር ነው።

የወያኔ ዘረኛነት በሃገራችን ከእዚህ ቀደም ታይቶ የማይታወቅ ርእዮተ አለማዊ ሽፋን ያለው ዘረኛነት እያስፋፋ ነው። በሃገሪቱ ውስጥ በሚገኙት ህዝቦች የስብእና መዋረድ፣ መራቆትና መደህየት፣ የሙብት ገፈፋና ረገጣ ወያኔ የሚያምንበት የትግራይነት ምንነት/ identity መገንቢያ ለማድረግ አቅዶ የሚንቀሳቀስ ነው። ይህንን ለማደረግ የታሪክ ጭብጦችን ማጣመም፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ከትግራይ ህዝብ ጋር የሚጋራው ታሪክ እንደሌለው መዋሸት ልማዱ ነው። ከእዚህም አልፎ ወያኔ ለአባላቱ የሚያስተላልፈው መልእክት ወርቅና ምርጦች ናችሁና ምርጥ ምርጡ ይገባችኋል የሚል ነው። ወያኔ እየሞከረ ያለው፤ የዘውግ አፓርታይድ/ Ethnic Apartheid በኢትዮጵያ በመገንባት በዘር አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ የተፈረጁ ዜጎች በአንድ ሃገር ላይ ለመፍጠር ነው።

ይህ የወያኔ መርሃ ግብር ምን ያህል ተሳክቷል የሚለው ጥያቄ ሳይንሳዊ መልስ የሚሰጠው ባይሆንም በእዚህ የወያኔ መሪዎች በእብደት የተሞላ እምነት እየተለከፈ ያለውን የሰው ቁጥር ለፖለቲካ ድለላ ብለን ማሳነሱ ተገቢ አይመስለኝም። ይህ መሰሪ የሆነ የወያኔ ድርጊት የማታ ማታ የሚኖረውን አስከፊ መዘዝ በሚገባ ተረድተው በግዜ ወያኔ ዘረኛ በሆነ መንገድ እየበከለ ያለውን የትግራይ ማህበረሰብና ወያኔ ዘረኛ በሆነ መንገድ በሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚያደርሰውን አይን ያወጣ በደል፣ ግፍና ዘረፋ መቃወም ያለባቸው በዋነኛነት እራሳቸው የትግራይ ተወላጆች ናቸው። የትግራይ ምሁራንና ዴሞክራት፣ የትግራይ የፖለቲካ ልሂቃን ከፍተኛ መስዋእትንት እየከፈሉም ቢሆን የወያኔንን ዘረኛ አደገኛ አመለካከትና ድርጊት በተግባር መታገል የሚገባቸው እነሱ ናቸው። ይህን የወያኔ አደገኛ አመለካከትና ድርጊት የሚኮንኑትን የሌሎች ዘውጌ ማህበረሰብ አባላት በጸረ ትግሬነት መኮነኑን ትተው በቅድሚ ማውገዝ የሚገባቸው የወያኔን ፋሽቶችንና ዘራፊዎችን ሊሆን ይገባል። የጸረ ዘረኛት የቤት ስራችንን ሁላችንም ተባብረን እንድንሰራ ከተፈለገ ይህንን የተቀደሰ የጋራ አላማ በዋንኛነት መምራት የሚገባቸው እነዚሁ አርቆ አሳቢ የትግራይ ምሁራንና ልሂቃን ናቸው የሚል እምነት አለኝ።

ሌሎቻችን ባለንበት ወቅት ማድረግ የሚገባን ጉዳይ ቢኖር ለራሳችን ክብር ደህንነት ቅድሚያ ሰጥተን ወያኔ በምንም አይንት መንገድ ዘረኛ በሆነ መንገድ አዋርዶ ሊገዛን የማንፈቅድለት መሆኑን በተግባር ማሳየት ነው። የዘረጋውን ዘረኛ ስርአት አወላለቅን በቦታው ሁሉንም ዜጎች፣ ወያኔ ነጻ አወጣዋለሁ የሚለውን የትግራይንም ህዝብ ጨምሮ በእኩልነት የሚያስተናግድ ፍትሃዊ ስርአት ለመመስረት ቆርጠን መነሳት ነው። ይህ አስቸጋሪ ትግል የሚጠይቀውን ማናቸውንም መስዋአትንት ለመክፈል መዘጋጀት ነው። በቃን የማለት ቁርጠኛነት መያዝ ማለት ነው።

ሌላው ከእዚህ የቁርጠኛነት ውሳኔ ጋር ማድርግ የሚገባን ነገር፤ ከወያኔ ዘረኛነት ምን ተምረናል የሚል ጥያቄ ማንሳት ነው። ይህ ጥያቄ በሃገራችን ልንፈጥረው የምንፈልገው የፖለቲካ ስርአት ወያኔ ከተደፈቀበት የዘረኛነት አደጋ እራሱን አንዴት መከላከል ይችላል? የሚል ሊሆን ይገባዋል።

ከወያኔ ዘረኛ አካሄድ መማር የሚገባን የወያኔ ዘረኛት ባስመረረን ቁጥር እያንዳንዳችን የራሳችንን በዘር ላይ የተመሰረተ አጥር በመስራት ችግሩን ልንፈታው የማንችል መሆኑን ነው። የዘር አጥር መገንባት የወያኔ ዘረኛነት በጋራ ለመታገል የምንችልበትን ጉልበት በታትነን ከሃገሪቱ ህዝብ 6 በመቶ የማይሞላውን ትግራይን እወክላለሁ ለሚል ኋላ ቀር ቡድን ራሳችንን መቀለጃ በማድርግ ለሚደርስብን ውርደት እራሳችንን ተባባሪዎች አደርገን ማቅረብ ይሆናል።

ከወያኔ ጋር የምናደርገውን ትግል እኛም እንደወያኔ በዘር ተከፋፈለን እንግፋው ብንል በዋንኛነት ተጠቃሚው ወያኔ ነው። በሃገራችን ሌላው ቀርቶ ሁለቱ ትልልቅ ዘውጌ ማህበራሰባት ኦሮሞውና አማራው ብቻ በወያኔ መረገጥ በቃን ብለው ቢነሱ፤ የተቀረቱንም ወያኔ የዘር ማጥፋት እርምጃ ሳይቀር የወሰደባቸውን አናሳ ዘውጌ ማህበራት ማስተባበር ቢችሉ፤ ወያኔ አስራ ስምንት አመት ቀርቶ አስራ ስምንት ወር ይህንን አይን ያወጣ ዘረኛ በሆነ መንገድ የተደራጀ ግፍና ዘረፋ እየፈጸመ መሰንበት የማይችል እንደነበር ማወቅ ይኖርብናል።

**ይቀጥላል**

**ወያኔ የመከላከያን ከፍተኛ በጀት ለትግራይ ክልል እንደ ተጨማሪ ልዩ በጀት አድርጎ ይጠቀማል፡፡ በሰራዊቱ ውስጥ ዘረኛ መድሎን ይፈጽማል፡፡ የትግራይ ሪፑብሊክ ምስረታ ህልሙንም አልረሳም፡፡** **ከገጽ 1 የዞረ**

3. ሌሎች ከቀለብ ውጭ በመደበኛ በጀት የሚገዙ አላቂና ቋሚ እቃዎች፣ የኤሌትሪክ ማሽነሪዎች ፣ የጽህፈት ዕቃዎች፣ ማንኛውም የቢሮና የመኖሪያ ቤት መገልገያ ዕቃዎችና የስልጠና መገልገያ ዕቃዎች፣ በሙሉ ከትግራይ ክልል ብቻ እንዲገዙ በመመሪያ ታዟል። ሌላው ቀርቶ ጠቅላላ የመከላከያ ወታደራዊ አገልግሎትና ሌሎች ጨርቃ ጨርቆች በሙሉ፣ ያለ ጨረታ አድዋ ከሚገኘው ከአልሜዳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ብቻ እንዲገዛ ተወስኖ፣ ተግባራዊ ከሆነ ብዙ አመታት አስቆጥሯል። ይህ ሰራዊት በአመት ሁለት ግዜ የደንብ ልብሱን እንዲቀይር ከወጣው መመሪያ ጋር ተደምሮ እነአልሜዳ ምን ያህል ገንዘብ ከመከላከያ ሚኒስቴር እንደሚዘርፉ ማየት ይቻላል፡፡

4. በኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት ጊዜ የጦርነቱን አጋጣሚ በመጠቀም 50000 (ሃምሳ ሽህ ) የትግራይ ሚሊሻ በጦርነቱ ትሳትፏል፣ ጦርነቱ ከቀጠለም ይዋጋሉ፣ በሚል ምክንያት ሥራ ላይ ሣይገኙ በየቤታቸው ተቀምጠው፣ በመከላከያ የደሞዝ መክፈያ ሰነድ፣ ከሰኔ 1991 ጀምሮ እስከ ሰኔ 1993 ዓ.ም ድረስ በተራ በወታደር ማዕረግ በወር 500.00 (አምስት መቶ ) ብር ተከፍሏቸዋል። ይህ አሰራር መቋረጡን ማወቅ የቻልንበት ማስረጃ የለም፡፡

5. በግንባር አካባቢ ወታደራዊ ልምምድ ሲደረግ ልምምዱ የገበሬዎች ሰብል አውድሟል፣ የግጦሽ ሳራቸውን ጎድቷል፣ አትክልታቸውን ሰባብሯል፣ በሚል ሰበብ የልተመጣጠነ ከፍተኛ ዋጋ ይከፈላል። ለምሳሌ አዲግራት ደንጎል አካባቢ፣ በሁለት ሄክታር መሬት ላይ የተዘራ ገብስ ላይ ‹‹የተወሰነ የእግረኛ ልምምድ ተደርጎበት ወደመ›› ተብሎ የግብርና ባለሙያዎች መጥተው ‹‹ከ30-40% ምርት ሊቀንስ ይችላል›› ብለው ሄዱ። ለሰዎቹ ግን የተሰጠው የካሳ ክፍያ 780000 (ሰባት መቶ ሰማኒይ ሺ) ብር ነበር። ይህ ገንዘብ ግን በሙሉ በተራው ገበሬ እጅ የገባ ሳይሆን ሰራዊቱን በዋንኛነት የሚቆጣጠሩትን የትግራይ ተወላጅ የሆኑ ከፍተኛ መኮንኖች ኪስ እንዳደለበ ይታወቃል፡፡

6. ሠራዊቱ በትግራይ ከተሞችና ገጠሮች በብዛት ሰፍሯል። በሠፈረባቸው አካባቢዎች ሁሉ ለመኖሪያ፣ ለቢሮና ለመጋዘኖች፣ ቤቶችን በውድ ዋጋ ተከራይቶ ይጠቀማል። ሰራዊቱ በሚኖርባቸው ቤቶች፣ ካምፖች፣ በሚገለገልባቸው ቢሮዎች ውስጥ ለቤት ሰራተኛነት፣ ለጽዳት ሰራተኛነትና ለሌሎችም ስራዎች የሚቀጠረው የአካባቢው ተወላጅ ቁጥር በትግራይ የስራ አጡን ቁጥር በመቀነስ ትልቅ ሚና አለው፡፡ ሰፊ የስራ መስክ ሆኗል፡፡

7. ሰራዊቱ በየወሩ ደሞዙን ተቀብሎ መልሶ የሚያወድመው በእዚሁ ክልል ውስጥ ስለሆነ ከሰራዊቱ የመዝናኛ ፍላጎቶች ጋር የተያያዙ ኢንዱስትሪዎች ከፍተኛ ተጠቃሚዎች የሆኑበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ እነዚህ ደግሞ በዋንኛነት በወያኔ ወይም በወያኔ አባላት የተያዙ ናቸው፡፡

8. ወያኔዎች የወታደሩን ነፃ ጉልበት ተጠቅመው ሠራዊቱን በአፈርን ውሃ ዕቀባ፣ በእርሻና በእርከን ሥራ በአረምና በአጨዳ ሥራ ይጠቀሙበታል።

9. የመከላከያን የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎችና ባለሙያዎች ክልሉ እንደፈለገ በነፃ ይጠቀምባቸዋል። ይህንን በመጠቀም በርካታ መንገዳች ተሰርተዋል። ግድቦች ተገንብተዋል።

10. ዘረኛነትንና አድሎን በተመለከተ ደግሞ የሚከተለው በደል ይፈጸማል። ከሰራዊቱ በተለያዩ ምክንያት የሚቀነሱ፣ በአካል መጉደል ወይም በሌሎች ምክንያቶች ሊሆን ይችላል፣ የሰራዊቱ አባላት መሃከል በዘር ላይ የተመሰረተ አድሎ ይፈጸማል፡፡ ከሌሎች ብሄረሰቦች የመጡ የሰራዊቱ አባላት የሚሰጣቸው ገንዘብ ከሚሰናበቱበት ግንባር ተነስተው ከሚኖሩበት ክልል የማያደርስ ነው፡፡ ለትግራይ ተወላጆች የሰራዊቱ ተቀናሾች ከመከላከያ ሚኒስቴር በጀት ወጪ እየተደረገ የሚሰጠው ካሳ በአስር ሽዎች ብር የሚቆጠር ብቻ ሳይሆን፣ እነዚህ የሰራዊቱ አባላት በተለያዩ ስራዎች መቀጠል እንዲችሉ የስልጠና የብድር ሌሎችም አስፈላጊ ግብአቶች ይሟሉላቸዋል፡፡ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ማብቂያ ከሰራዊቱ በተለያዩ ምክንያቶች የተቀነሱ የሌሎች ብሄረሰብ አባላት የተሰጣቸው ገንዘብ በግለሰብ ደረጃ ከ2000 እስከ 3000 ብር የሚደርስ ብቻ ነበር፡፡ ለትግራይ ተወላጆች ግን ከ30 እስከ 40 ሽህ ብር ነበር፡፡ ሌሎቹ ከሰራዊቱ ከተበተኑ በኋላ ምንም አይነት የመቋቋሚ ድጋፍ ያልተደረገላቸው ሲሆን የትግራይ ብሄረሰብ ለሆኑ የሰራዊቱ አባላት ግን የሚደረገው አጠቃላይ የማቋቋሚ ድጋፍ በብዙ ሚሊዮን ብሮች በሚሰላ ሃብት የተደገፈ ነው፡፡ ይህን አሳዛኝ ዘረኛ አድሎ ወያኔ የሚፈጸመው ወያኔ እንደሚለው 70 ሽህ ዜጎች ሳይሆን 98ሽ ዜጎች ትግራይ ምድር ድረስ ተጉዘው መለስ ዜናዊ ‹‹ለወላይታው ምኑ ነው›› ያለውን የአክሱም ሃውልት ምድር ለመከላከል በረገፉበት ዘግናኝ ጦርነት ማግስት ነበር፡፡ እግረ መንገዳችንን በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ከሞቱት መሃል አብዛኛው አማሮች ሲሆኑ ከስምንት ሽህ በላይ የሚሆኑ የአፋር ተወላጆች በእዚህ ጦርነት ውድ ህይወታቸውን መክፈላቸውን ማወቅ ችለናል፡፡ አጅግ በርካታ የሆኑ የአካል ጉዳተኞችም ያለምንም ድጋፍ በየክልሎቹ ተበትነው፤ በጦርነት የተቆረጠ እግራቸውንና እጃቸውን መለመኛ አድርገው የመከራ ኑሮአቸውን ይገፋሉ፡፡ በሰዎች መታወቂያ ላይ ሳይቀር የዜጎችን ዘር ለመጻፍ ድፍረቱ ያለው አገዛዝና በሆነ ባለሆነ ስለብሄራዊ ተዋጽኦ ዲስኩር መስጠት የሚቀናቸው የወያኔ ባለስልጣናት ለምን በየጦርነቱ አውድማ የሚማግዱተን የህዝብ ቁጥርና የሚቾቹንና የተጎጂዎችን ብሄራዊ ተዋጽኦ ሊነግሩን እንደማይፈቅዱ ከእዚህ መረጃ መገንዘብ ይቻላል ፡፡

**ለማጠቃለል፡** ወያኔ የኢትዮ - ኤርትራ ፍጥቻ እንዲቀጥል የሚያደርገው፣ አብዛኛውን የሃገሪቱን የመከላከያ ሃይል በቀላሉ ሊቆጣጠረው ከሚችልበት አካባቢ ለማስቀመጥ እድል እንደሚሰጠው ስለሚያውቅ ነው፡፡ የኢትዮ-ኤርትራ ፍጥጫ እስከቀጠለ ድረስ የሃገሪቱ መከላከያ ሃይል ቁጥሩም በጀቱም አይቀንስም፡፡ የሚሰፍረውም በትግራይ ውስጥ ይሆናል፡፡ ይህ ማለት ከአመት አመት የመከላከያ በጀት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከላይ በጠቀስናቸው መንገዶች በትግራይ ክልል የሚደረገውን የልማት ስራ አጋዥ ሆኖ ይቀጥላል፡፡ ይህንን ጠባብ፣ ዘረኛና ዘራፊ የሆነ የወያኔ ቡድን ፍላጎት እስካሟላ ድረስ፣ ኢትዮጵያ ከድህነቷ ጋር የማይመጣጠን ትልቅ የመከላከያ ሃይል ተሸክማ ኖረች አልኖረች ወያኔን አያሳስበውም፡፡ ወያኔ ሌላው የኢትዮ -ኤርትራ ፍጥጫ እንዲቀጥል የሚፈልግበት ምክንያት፣ ወደፊት ወያኔ በተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ሊፈጽም ላሰበው ወንጀል የመከላከያ ሃይሉን የጦር መሳሪያዎች በቀላሉ መጠቀሚያ ለማድርግ በሚያመች ቦታ ማከማቸት ስላስቻለው ነው፡፡ ዛሬ የሃገሪቱ የመከላከያ ሃይል፣ አየር ሃይሉ በሙሉ፣ ሜካናይዝድ ብርጌዱ ከነዘመናዊ ታንኮቹና መድፎቹ፣ በሰራዊት ውስጥ አለ የተባለው ሌላ ዘመናዊ መሳሪያ በሙሉ የሚገኘው በትግራይ ክልል ነው፡፡

በወያኔ የፖለቲካ ስሌት ውስጥ የኢትዮጵያ ህዝብ በወያኔ ዘረኛነትና ዘራፊነት ላይ ተንገፍግፎ ከተነሳ ትግራይን ከነሙሉ የሃይል ማመንጫዎቿ፣ በኤፈርት ዘረፋ ከተሰባሰበው ታላቅ የገንዘብ ካፒታል ጋር፣ በኤርትራ ፍጥጫ ስም በክልሏ ወያኔ እንዲከማች ካደረገው የሃገሪቱ ወታደራዊ ድርጅትና ዘመናዊ የተሟላ የጦር መሳሪያ ጋር፣ በዘር አድሎ ላይ በተመሰረተ የሃገር ውስጥና የውጭ ትምህርትና የሙያ ስልጠና ሲሰጣቸው ከኖሩት የጦርና የሲቪል ሙያተኞች ጋር ከኢትዮጵያ ገንጥሎ፣ እነመለስ ዜናዊ የነገሱባት ነጻ የትግራይ ሪፑብሊክ ለማወጅ ይቻላል የሚል ስሌት ጨምሮ እንደሆነ መረዳት ይገባል፡፡ ወያኔ ከሌሎች ብሄርና ብሄረሰብ የመጡትን የሰራዊት አባላት ከትግራይ አባሮ የሃገሪቱን መከላከያ ሃይል ሙሉ በሙሉ ይዞ ያለምንም መከላከያ ሃይልና መሳሪያ ባዶውን የቀረውን የኢትዮጵያ ህዝብ እንዳሻው እያስፈራራና እያሸበረ በነጻይቱ ትግራይ ላይ ተረገጋቶ የመኖር ተለዋጭ እቅድ ያለው ዘረኛ አገዛዝ መሆኑን መላ የኢትዮጵያ ህዝብ በግዜ ማወቅ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

## መለስ ዜናዊ በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ግንቦት 7ትን እንዳይቀላቀሉ በመሬት በመስጠት ለመደለል የሚያደርገው ጥረት ተቀባይነት እንደሌለው ተገለጸ

የግንቦት 7 ከፍተኛ አመራር አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ለንቅናቄው ድምጽ በሰጡት ቃለምልልስ ‹‹የመለስ ዜናዊ የቤተሰብ ታሪክም ይሁን በአገሪቱ ላይ እያደረሰ ያለው ጥፋት፣ መሬት ለማከፋፈል የሞራል ብቃት አይሰጠውም›› ሲሉ ተናግረዋል፡፡ አቶ አንዳርጋቸው በዚሁ ቃለ ምልልስ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ደክመው ያገኙትን ሀብት ባልተረጋጋ ሥርዓት ውስጥ እንዳያፈሱ መክረው፣ በማጭበርበርና በተለያዩ መንገዶች የመለስ የዘረፋ ታሪክ ተባባሪ የሚሆኑት ከተጠያቂነት እንደማያመልጡ አስገንዝበዋል።

የመለስ ቡድን በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን በሽብረተኝነት ስም ለማስፈራራት የሚያደርገው ሙከራ በውጭ መንግስታት በኩል ተቀባይነት ማጣቱን የተናገሩት አቶ አንዳርጋቸው፣ የውጭ መንግስታት ከግንቦት 7 ይልቅ የመለስን አገዛዝ አሸባሪ አድርገው እንደሚመለከቱት ገልፀዋል።

ከኤርትራ ጋር በተያያዘ ለተነሱ ጥያቄዎች ሲመልሱም ወያኔ ግንቦት7ን ከኤትራ መንግሥት ጋር በሚፈጥረው ግንኙነት ለመክሰስ የሞክራል ብቃቱ እንደሌለው፤ ይልቁንም ወያኔን አዲስ አበባ ያደረሰው የሻእቢያ ኃይል መሆኑን አስታውሰው፤ በኤርትራ ውስጥ መነሻቸውን አድረገው ትግል የጀመሩ ድርጅቶች እስካሁን ለምን ለውጤት እንዳልበቁ በቅድሚያ ራሳቸውን መገምገም እንዳለባቸው ተናግረዋል። አንዳንድ ሰዎች ግንቦት 7 የሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች እጣ ፋንታ ይደርሰዋል እያሉ የሚናገሩት የትግሉን ባህሪ ባለመረዳት ነው ያሉት አቶ አንዳርጋቸው፣ የግንቦት7 የትግል ሜዳ መላው ኢትዮጵያ እንጅ የኤርትራ መሬት እንዳልሆነ ተናግረዋል።

## የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከአገር ጥቅም ይልቅ ከገጽ 2 የዞረ

የአስተዳደርና ፋይናንስ ክፍል ውስጥ ተመድቤ ነበር። የምሰራውና የምኖረው ግን በሰቀቀን ነበር።የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች እንደጦር ሜዳ የሚመሩት በወያኔ ታጋዮች ነው። የየመን አምባሳደር ቶፊቅ አብዱላሂ የሃረሪ ተወላጅ ሲሆን የወያኔው አገዛዝ ለይስሙላ የብሄር ተዋጽኦ በሚል ሰበብ የጎለተውና በወያኔ ካድሬዎች መመሪያ የሚሰራ ነው። አምባሳደሩ በንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሲሆን አሁንም ከየመን እና ኤምባሲው ከሚሸፍናቸው ኢራን፣ ፓኪስታንና አማን ሃብታም ነጋዴዎች ጋር በመመሳጠር ዘመዶቹን በሸርክና እያጣመረ ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት የናጠጠ ነጋዴ ሆኗል›› ይላሉ።

አምባሰደሩ ለይስሙላ ይቀመጥ እንጂ ኤምባሲውን የሚያሽከረክሩት ጌታቸው ተፈሪ፣ ደስታ ካህሳይ፣ አደምኑር መሓሙድ እና አብዱል ቃዴር ርዝቁ የተባሉ የትግራይ ብሄር ተወላጅ የሆኑ ታጋዮች ናቸው የሚሉት ዲፕሎማቱ፣ ታጋዮቹም በስለላ ሙያ ላይ ተሰማርተው ይሰሩ እንደነበር አጋልጠዋል።

በተያያዘ ዜና ኢትዮጵያ በአለም ዙሪያ ካሏት 38 የዲፕሎማቲክ ሚሽን ጽ/ቤቶች ውስጥ በ35ቱ ውስጥ እየሰሩ ያሉ ሰዎች ስም ዝርዝር፣ ብሄር፣ የትምህርት ደረጃ፣ ደምወዝና ከወያኔ ቱብ ቱባ ባለስልጣናት ጋር ያላቸው የዝምድና ሃረግ ጭምር የሚያጋልጥ ዘገባ እየተዘጋጀ መሆኑን የግንቦት 7 የመረጃ ጥናት ቡድን አስታውቋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ እና በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ፆይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org